


የመጨረሻው ቀን

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

33÷21 ለእናንተ *አላህን እና "የመጨረሻውን ቀን" የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አላችሁ*። لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ اللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُو اللَّهَ وَالْيَوْمَ الْآخِرَ وَذَكَرَ اللَّهَ كَثِيرًا

“ዱንያ” دُّنْيَا ማለት “ቅርቢቱ” ማለት ሲሆን የምንኖርበት ይህንን ዓለም ያመለክታል÷ “አኺራህ” آخِرة ማለት “መጨረሻይቱ” ማለት ሲሆን የሚቀጥለውን ዓለም ያመለክታል። የዚህ ዓለም የሚያበቃበት ቀን "የመጨረሻው ቀን ነው። "የመጨረሻው ዘመን ጥናት”Eschatology” በኢሥላም “አል-አኺሩ አዝ-ዘማን” الْزَمَان الْآخِر ይባላል÷ በቁርኣን "የውመል አኺር" يَوْم الْآخِر ማለትም "መጨረሻው ቀን" ተብሎ ብዙ ቦታ ተጠቅሷል÷ ከስድስቱ አርካኑል ኢማን መካከልም አንዱ "በመጨረሻው ቀን" ማመን ነው፦

33÷21 ለእናንተ *አላህን እና "የመጨረሻውን ቀን" የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አላችሁ*። لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ اللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُو اللَّهَ وَالْيَوْمَ الْآخِرَ وَذَكَرَ اللَّهَ كَثِيرًا

ጃምዒ አት-ቲርሚዚይ መጽሐፍ 40, ሐዲስ 5

ዑመር ኢብኑ ኸጣብ እንዳስተላለፈው፦ “አንድ በጣም ነጭ ልብስ የለበሰና በጣም ጥቁር ጸጉር ያለው ሰው በመጣ ጊዜ ከአላህ መልእክተኛ” ﷺ “ጋር ነበርን፤ ወደ እርሳቸው ሲጓዝ አይታይም ነበር፤ ወደ ነብዩ”

ﷺ" እስከሚደርስ ድረስ ከእኛ መካከል ማንም ዐላወቀውም፤ ጉልበቱን በእራሳቸው ጉልበት ተቃራኒ አድርጎ ከዚያም እንዲህ አለ፦ *"ሙሐመድ ሆይ! ኢማን ምንድን ነው? እርሳቸውም፦ "በአላህ ማመን፣ በመላእክቱ ማመን፣ በመጽሐፍቱ ማመን፣ በነቢያቱ ማመን፣ በመጨረሻው ቀን ማመን እና በሰናይ እና እኩይ ቀደር ማመን ነው" አሉ*። قَالَ عُمَرُ بْنُ الْخَطَّابِ كُنَّا عِنْدَ رَسُولِ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم فَجَاءَ رَجُلٌ شَدِيدُ بَيَاضِ الثِّيَابِ شَدِيدُ سَوَادِ الشَّعَرِ لاَ يُرَى عَلَيْهِ أَثَرُ السَّفَرِ وَلاَ يَعْرِفُهُ مِنَّا أَحَدٌ حَتَّى أَتَى النَّبِيَّ صلى الله عليه وسلم فَأَلْزَقَ رُكْبَتَهُ بِرُكْبَتِهِ ثُمَّ قَالَ يَا مُحَمَّدُ مَا الإِيمَانُ قَالَ " أَنْ تُؤْمِنَ بِاللَّهِ وَمَلاَئِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ وَالْيَوْمِ الآخِرِ وَالْقَدَرِ خَيْرِهِ وَشَرِّهِ

"የውም" يَوْم ማለት "ቀን" ማለት ሲሆን መአልት እና ሌሊት ያቀፈ የሀያ አራት ሰዓት እርዝማኔ ብቻ ሳይሆን ፍርድ የሚከናወንበት አንድ ሺህ ዓመት ያመለክታል፦

22÷47 አላህም ቀጠሮውን በፍጹም የማይጥስ ሲሆን በቅጣት ያቻኩሉሃል። *"እጌታህም ዘንድ አንዱ ቀን ከምትቆጥሩት ቀን እንደ ሺሕ ዓመት ነው"*። وَيَسْتَعْجِلُونَكَ بِالْعَذَابِ وَلَن يُخْلِفَ اللَّهُ وَعْدَهُ ۚ وَإِنَّ يَوْمًا عِندَ رَبِّكَ كَأَلْفِ سَنَةٍ مِّمَّا تَعُدُّونَ

32÷5 *"ነገሩን ሁሉ ከሰማይ ወደ ምድር ያዘጋጃል። ከዚያም ከምትቆጥሩት ዘመን ልኩ ሺህ ዓመት በሆነ ቀን ውስጥ ወደ እርሱ ይወጣል"*። يُدَبِّرُ الْأَمْرَ مِنَ السَّمَاءِ إِلَى الْأَرْضِ ثُمَّ يَعْرُجُ إِلَيْهِ فِي يَوْمٍ كَانَ مِقْدَارُهُ أَلْفَ سَنَةٍ مِّمَّا تَعُدُّونَ

ይህ የመጨረሻ ቀን፦

"የውመል መውዑዱ" يَوْم الْمَوْعُودِ

"የውሙል ሐቅ" يَوْمُ الْحَقّ

"የውሙል ኹሩጅ" يَوْمُ الْخُرُوج

"የውመል ቂያማህ" يَوْمَ الْقِيَامَة
"የውሚድ-ዲን" يَوْمِ الدِّين
"የውመል ፈትሕ" يَوْمَ الْفَتْح
"የውመል ጀምዕ" يَوْمِ الْجَمْع
"የውሙል ፈስል" يَوْمُ الْفَصْل
"የውመት ተላቅ" يَوْمَ التَّلَاق
"የውሚል ሒሣብ" يَوْمِ الْحِسَاب
"የውመት ተናድ" يَوْمَ التَّنَاد
"የውሙል ወዒድ" يَوْمُ الْوَعِيد
"የውመል ሐሥራህ" يَوْمَ الْحَسْرَة
"የውሙም መሽሁድ" يَوْمٌ مَّشْهُود
"የውሙል ኹሉድ" يَوْمُ الْخُلُود ተብሏል።
ይህንን ጥርስ እና ምላሱን እየነቀስን ኢንሻላህ ነጥብ በነጥብ እናያለን፦

ነጥብ አንድ

"የውመል መውዑድ"
"የውመል መውዑድ" يَوْم الْمَوْعُودِ ማለት "የተቀጠረው ቀን" ማለት ነው፦
85÷2 *"በተቀጠረው ቀንም እምላለው"*። وَالْيَوْمِ الْمَوْعُودِ

አላህ ፍጥረትን ወሮታና አጸፌታ÷ ምንዳና ትሩፋት የሚከፍበትን ቀን ቀጥሯል። ይህ ቀጠሮ መጪ ነው÷ በዚያ ቀን ሰማዩ ተሰንጣቂ ነው÷ ቀጠሮው ተፈጻሚ ነው። ከሃድያን ቢዚያ ቀን፦ "ይህ ያ አዛኙ ጌታ በእርሱ የቀጠረን መልክተኞቹም እውነትን የነገሩን ነው" ይላሉ፦

29÷5 *የአላህን መገናኘት ተስፋ የሚያደርግ ሰው ይዘጋጅ። የአላህ ቀጠሮ በእርግጥ መጪ ነውና*። እርሱም ሰሚው ዐዋቂው ነው። مَن كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ اللَّهِ فَإِنَّ أَجَلَ اللَّهِ لَآتٍ ۚ وَهُوَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ

34÷30 *«ለእናንተ ከእርሱ አንዲትንም ሰዓት የማትዘገዩበት የማትቀድሙበትም የቀጠሮ ቀን አላችሁ» በላቸው*። قُل لَّكُم مِّيعَادُ يَوْمٍ لَّا تَسْتَأْخِرُونَ عَنْهُ سَاعَةً وَلَا تَسْتَقْدِمُونَ

73÷18 *"ሰማዩ በእርሱ በዚያ ቀን ተሰንጣቂ ነው። ቀጠሮው ተፈጻሚ ነው*። السَّمَاءُ مُنفَطِرٌ بِهِ ۚ كَانَ وَعْدُهُ مَفْعُولًا

36፤52 *«ወይ ጥፋታችን! ከመኝታችን ማን ቀሰቀሰን? ይህ ያ አዛኙ ጌታ በእርሱ የቀጠረን መልክተኞቹም እውነትን የነገሩን ነው» ይላሉ*። قَالُوا يَا وَيْلَنَا مَن بَعَثَنَا مِن مَّرْقَدِنَا ۖ هَٰذَا مَا وَعَدَ الرَّحْمَٰنُ وَصَدَقَ الْمُرْسَلُونَ

ነጥብ ሁለት

"የውሙል ሐቅ"

"የውሙል ሐቅ" يَوْمُ الْحَقّ ማለት "የተረጋገጠ ወይም የእውነት ቀን" ማለት ነው፦

78÷39 *ይህ የተረጋገጠው ቀን ነው። የሻም ሰው ወደ ጌታው መመለስን ይይዛል*። ذَٰلِكَ الْيَوْمُ الْحَقُّ ۖ فَمَن شَاءَ اتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِ مَآبًا

“አል-የቂን” الْيَقِين ማለት “እርግጠኝነት” ማለት ሲሆን በሦስት ይከፈላል፥ እርሱም፦

“ዒልመል የቂን” عِلْمَ الْيَقِين ማለትም "እርግጠኛ ዕውቀት"

“ዐይነል የቂን” عَيْنَ الْيَقِين ማለትም "እርግጠኛ ማየት"

“ሐቁል የቂን” حَقُّ الْيَقِين ማለትም "እርግጠኛ እውነት" ነው።

አማንያን ጀነት ውስጥ ያለው ጸጋ መቅመስ÷ ከሃድያን ጀሃነም ውስጥ ያለው ቅጣት መቅመስ ሐቁል የቂን ነው÷
77÷43 *«ትሠሩት በነበራችሁት ዋጋ የምትደሰቱ ኾናችሁ ብሉ፣ ጠጡም፤» ይባላሉ*። كُلُوا وَاشْرَبُوا هَنِيئًا بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ
46÷34 *እነዚያም የካዱት ሰዎች በእሳት ላይ በሚቀረቡ ቀን «ይህ እውነት አይደለምን?» ይባላሉ። «እውነት ነው፤ በጌታችን ይኹንብን» ይላሉ። አላህም «ትክዱ በነበራችሁት ምክንያት ቅጣቱን ቅመሱ» ይላቸዋል”*። وَيَوْمَ يُعْرَضُ الَّذِينَ كَفَرُوا عَلَى النَّارِ أَلَيْسَ هَـٰذَا بِالْحَقِّ ۖ قَالُوا بَلَىٰ وَرَبِّنَا ۚ قَالَ فَذُوقُوا الْعَذَابَ بِمَا كُنتُمْ تَكْفُرُونَ

ነጥብ ሦስት

"የውሙል ኹሩጅ"

"የውሙል ኹሩጅ" ጂ يَوْمُ الْخُرُوج ማለት "የመውጫው ቀን ነው" ማለት ነው÷ ጠሪው መልአክ በሚጠራበት ቀን ሰዎች ከመቃብራቸው ይወጣሉ÷
53÷6 ከእነርሱም ዙር። *ጠሪው መልአክ ወደ አስደንጋጭ ነገር የሚጠራበትን ቀን አስታውስ*። فَتَوَلَّ عَنْهُمْ ۘ يَوْمَ يَدْعُ الدَّاعِ إِلَىٰ شَيْءٍ نُّكُرٍ
50÷41 *"የሚነገርህን አዳምጥም። ጠሪው ከቅርብ ስፍራ በሚጠራበት ቀን ከመቃብራቸው ይወጣሉ*። وَاسْتَمِعْ يَوْمَ يُنَادِ الْمُنَادِ مِن مَّكَانٍ قَرِيبٍ
50÷42 *ጩኸቲቱን በእውነት የሚሰሙበት ቀን ያ ከመቃብር "የመውጫው ቀን" ነው*። يَوْمَ يَسْمَعُونَ الصَّيْحَةَ بِالْحَقِّ ۚ ذَٰلِكَ يَوْمُ الْخُرُوجِ
30÷25 *ሰማይና ምድርም በትዕዛዙ መቆማቸው እና ከዚያም *ከምድር ጥሪን በጠራችሁ ጊዜ እናንተ ወዲያውኑ የምትወጡ መሆናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው*። وَمِنْ آيَاتِهِ أَن تَقُومَ السَّمَاءُ وَالْأَرْضُ بِأَمْرِهِ ۚ ثُمَّ إِذَا دَعَاكُمْ دَعْوَةً مِّنَ الْأَرْضِ إِذَا أَنتُمْ تَخْرُجُونَ

"የምትወጡ" ለሚለው የገባው ቃል "ተኽሩጁነ" تَخْرُجُونَ መሆኑን አንባቢ ልብ ይለዋል። ጠሪው መልአክ የሚጣራበት የመጀመሪያው መነፋት ወደ አስደንጋጭ ነገር የሚጠራበትን ሲሆን ሁለተኛው መነፋት ሰዎች ከመቃብራቸው የሚወጡበት ነው፦

39÷68 *በቀንዱም ይነፋል÷ በሰማያት ውስጥ ያለው ፍጡር እና በምድርም ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ አላህ የሻው ሲቀር በድንጋጤ ይሞታል። ከዚያም በእርሱ ሌላ መንነፋት ይነፋል÷ ወዲያውም እነርሱ የሚሠራባቸውን የሚጠባበቁ ኾነው ቋሚዎች ይኾናሉ*። وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَصَعِقَ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَمَن فِي الْأَرْضِ إِلَّا مَن شَاءَ اللَّهُ ۖ ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ أُخْرَىٰ فَإِذَا هُمْ قِيَامٌ يَنظُرُونَ

36÷51 *"በቀንዱም ይነፋል÷ ወዲያውኑም እነርሱ ከመቃብሮቻቸው ወደ ጌታቸው በፍጥነት ይገሰግሳሉ*። وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَإِذَا هُم مِّنَ الْأَجْدَاثِ إِلَىٰ رَبِّهِمْ يَنسِلُونَ

ይህ በመለከት ሁለቱን መነፋት የሚነፋው መልአክ "ሷሒቡ አስ-ሱር" صَاحِب الصُّور ማለት "የመለከት ባለቤት" የመላእክት አለቃ ኢሥራፊል ነው።

ነጥብ አራት

"የውመል ቂያማህ"

“ቂያማህ” قِيَٰمَة የሚለው ቃል “ቃመ” قَامَ ማለትም “ተነሣ” ወይም “ቆመ” ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን “ትንሣኤ” ማለት ነው። "የውመል ቂያማህ" يَوْمَ الْقِيَامَة ማለት "የትንሣኤ ቀን" ማለት ነው÷ አምላካችን አላህ ስለ ትንሳኤ አጽንዖትና አንክሮት ለመስጠት በትንሣኤ ቀን ምሏል፦

75÷1 *"ነገሩ ከሓዲዎች እንደሚሉት አይደለም። *"በትንሣኤ ቀን እምላለሁ"*። لَا أُقْسِمُ بِيَوْمِ الْقِيَامَةِ
23÷16 *"ከዚያም እናንተ "በትንሣኤ ቀን" ትቀሰቀሳላችሁ"*። ثُمَّ إِنَّكُمْ يَوْمَ الْقِيَامَةِ تُبْعَثُونَ
39÷68 *"ከዚያም በእርሱ ሌላ መንነፋት ይነፋል÷ ወዲያውም እነርሱ የሚሠራባቸውን የሚጠባበቁ ኾነው "ቋሚዎች" ይኾናሉ*። ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ أُخْرَىٰ فَإِذَا هُمْ قِيَامٌ يَنظُرُونَ

"ቃኢም" قَآئِم ማለት "ቃሚ" ማለት ነው÷ የቃኢም ብዙ ቁጥር ደግሞ "ቂያም" قِيَام ማለት ሲሆን "ቋሚዎች" ማለት ነው። ትንሳኤ እንዳለ በዕውቀት ያወቁ እና በእምነት ያመኑ የዕውቀት እና የእምነት ባለቤቶች እነዚያ የካዱትን በትንሳኤ ቀን÷ "ይህም የካዳችሁት የትንሣኤ ቀን ነው። ግን እናንተ የማታውቁ ነበራችሁ" ይሏቸዋል÷ እነዚያ የካዱት በትንሣኤ ቀን ሙስሊሞች በኾኑ ኖሩ በብዛት ይመኛሉ። እነርሱ "ከአላህ ሌላ አምላክ የለም" በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ÷
30÷56 *እነዚያንም ዕውቀትንና እምነትን የተሰጡት «በአላህ መጽሐፍ (ፍርድ) እስከ ትንሣኤ ቀን በእርግጥ ቆያችሁ። ይህም የካዳችሁት የትንሣኤ ቀን ነው። ግን እናንተ የማታውቁ ነበራችሁ» ይሏቸዋል*። وَقَالَ الَّذِينَ أُوتُوا الْعِلْمَ وَالْإِيمَانَ لَقَدْ لَبِثْتُمْ فِي كِتَابِ اللَّهِ إِلَىٰ يَوْمِ الْبَعْثِ ۖ فَهَٰذَا يَوْمُ الْبَعْثِ وَلَٰكِنَّكُمْ كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ
15÷2 *"እነዚያ የካዱት በትንሣኤ ቀን ሙስሊሞች በኾኑ ኖሩ በብዛት ይመኛሉ"*። رُّبَمَا يَوَدُّ الَّذِينَ كَفَرُوا لَوْ كَانُوا مُسْلِمِينَ
37÷35 *እነርሱ "ከአላህ ሌላ አምላክ የለም" በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ*። إِنَّهُمْ كَانُوا إِذَا قِيلَ لَهُمْ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللَّهُ يَسْتَكْبِرُونَ

ነጥብ አምስት

"የውሚድ ዲን"

“ዲን” دِين የሚለው ቃል “ዳነ” دَانَ ማለትም “ፈረደ” “በየነ” ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን “ሃይማኖት” “ፍትሕ” “ፍርድ” “ሕግ” “መርሕ” ማለት ነው። "የውሚድ ዲን" يَوْمِ الدِّين ማለት "የፍርዱ ቀን" ማለት ነው፦

1÷4 *"የፍርዱ ቀን" ባለቤት ለኾነው"*። مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ

37÷20 *«ዋ ጥፋታችን! ይህ "የፍርዱ ቀን" ነው» ይላሉም*። وَقَالُوا يَا وَيْلَنَا هَـٰذَا يَوْمُ الدِّينِ

56÷6 *"ፍርድን ማግኘትም የማይቀር ነው"*። وَإِنَّ الدِّينَ لَوَاقِعٌ

እዚህ አንቀጽ ላይ "ፍርድ" ለሚለው ቃል የገባው በአመልካች መስተአምር "አድ-ዲን" الدِّين መሆኑ አንባቢ ልብ ይለዋል። “ዲን” دِين ሦስት ደረጃ አለው፥ እርሱም፦

“ኢሥላም” إِسْلَام

“ኢማን” إِيمَان

“ኢሕሣን” إِحْسَان ናቸው።

ዲን ለአላህ ብቻ በማጥራት አላህን ማምለክ ነው፦

39÷11 በል «እኔ *አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ያጠራሁ ኾኜ እንዳመልከው ታዘዝኩ"*። قُلْ إِنِّي أُمِرْتُ أَنْ أَعْبُدَ اللَّهَ مُخْلِصًا لَّهُ الدِّينَ

እዚህ አንቀጽ ላይ "ያጠራ" ለሚለው ቃል የገባው "ሙኽሊስ" مُخْلِص ነው። "ኢኽላስ" إِخْلَاص የሚለው ቃል "ኸለሰ" خَلَصَ ማለትም "ጠራ" ከሚለው ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን ከእዩልኝ እና ከስሙልኝ፥ ከወቀሳ እና ከሙገሳ ነጻ ሆኖ ዲንን ለአላህ ብቻ "ማጥራት" ማለት ነው። ዒባዳን በኢኽላስ የሚሠራ ሙሥሊም "ሙኽሊስ" مُخْلِص ይባላል። አላህ ዘንድ

ዲን ኢሥላም ብቻ ነው÷ ከኢሥላም ዲን ሌላ ዲንን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከእርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።

3÷19 *አላህ ዘንድ ሃይማኖት ኢሥላም ብቻ ነው*። إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ

3÷85 *ከኢሥላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከእርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው*። وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الْآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ

ነጥብ ስድስት

"የውመል ፈትሕ"

"የውመል ፈትሕ" حَتْفَ الْيَوْمَ ማለት "የፍርድ ቀን" ማለት ነው÷ በቁርኣን ከተገለጹ የአላህ ስሞች መካከል "አል-ፈታሕ" حَتَّاحُ الْفَ ማለትም "ፈራጁ" ነው።

32÷29 *«"በፍርድ ቀን" እነዚያን የካዱትን ሰዎች እምነታቸው አይጠቅማቸውም። እነርሱም ጊዜን አይሰጡም»* በላቸው። قُلْ يَوْمَ الْفَتْحِ لَا يَنفَعُ الَّذِينَ كَفَرُوا إِيمَانُهُمْ وَلَا هُمْ يُنظَرُونَ

34÷26 *«ጌታችን በመካከላችን ይሰበስባል። ከዚያም በመካከላችን በእውነት ይፈርዳል። እርሱም በትክክል ፈራጁ ዐዋቂው ነው»* በላቸው። قُلْ يَجْمَعُ بَيْنَنَا رَبُّنَا ثُمَّ يَفْتَحُ بَيْنَنَا بِالْحَقِّ وَهُوَ الْفَتَّاحُ الْعَلِيمُ

"ፈትሕ" فَتْحَ የሚለው ቃል "ፈተሐ" فَتَحَ ማለትም "ከፈተ" ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "መክፈት" ማለት ነው÷ "መፋቲሕ" مَفَاتِح ማለት እራሱ "መክፈቻ" ማለት ነው። ቁርኣን ላይ ተመሳሳይ ቃል ቢኖረው እንኳን ተመሳሳይ አሳብና ትርጉም አለው ማለት አይደለም÷

የአንድን ቃል አማራጭ ትርጉም የሚወስነው ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ እንደ ሆነ ቅቡል ነው። መታየት ያለበት ቃሉ ሳይሆን ቃሉ የወከለው አሳብ ነው÷ እዚህ ዐውድ ላይ "ፈትሕ" فَتْح ማለት "ፍርድ" ማለት ነው፦

26÷118 *«በእኔ እና በእነርሱም መካከል ፍርድን "ፍረድ"! አድነኝም!። ከእኔ ጋር ያሉትን ምእምናንም።»* فَافْتَحْ بَيْنِي وَبَيْنَهُمْ فَتْحًا وَنَجِّنِي وَمَن مَّعِيَ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ

እዚህ አንቀጽ ላይ "ፍረድ" ለሚለው ግስ የገባው ቃል "ኢፍተሕ" افْتَحْ መሆኑ አንባቢ ልብ ይለዋል። በፍርድ ቀን ለካፊር ይፈረድበታል÷ ለሙእሚን ይፈረድለታል።

ነጥብ ሰባት

"የውሙል ጀምዕ"

"የውመል ጀምዕ" يَوْم الْجَمْع ማለት "የመሰብሰቢያውንም ቀን" ማለት ነው፦

42÷7 እንደዚሁም የከተሞች እናት የኾነችውን እና በአካባቢዋ ያሉትንም ልታስጠነቅቅ *የመሰብሰቢያውንም ቀን በእርሱ ጥርጣሬ የሌለበት ሲኾን ልታስጠነቅቅ ዐረብኛ የኾነን ቁርኣን ወደ አንተ አወረድን*። وَكَذَٰلِكَ أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ قُرْآنًا عَرَبِيًّا لِّتُنذِرَ أُمَّ الْقُرَىٰ وَمَنْ حَوْلَهَا وَتُنذِرَ يَوْمَ الْجَمْعِ لَا رَيْبَ فِيهِ

“አሐድ” أَحَد ማለት “አንድ” ማለት ነው፤
“ኢስነይን” اِثْنَيْن ማለት “ሁለት” ማለት ነው፤
“ሱላሳእ” ثُّلَاثَاء ማለት “ሦስት” ማለት ነው፤

“አርቢዓእ” أَرْبِعَاء ማለት “አራት” ማለት ነው፣
“ኸሚሥ” خَمِيس ማለት “አምስት” ማለት ነው፣
“ጁሙዓህ” جُمُعَة ማለት ደግሞ “ስብስብ” ማለት ነው÷ "የውሙል ጁሙዓህ" يَوْمُ الْجُمُعَة ማለት እራሱ "የስብስብ ቀን" ማለት ነው። አደም የተፈጠረው በጁሙዓህ ቀን ነው÷ ቂያማህ የሚቆመውም በጁሙዓህ ቀን ነው፦

ጃምዒ አት-ቲርሚዚይ መጽሐፍ 4, ሐዲስ 1

አቡ ሁራይራህ እንደተረከው፦ "ነቢዩ" ﷺ " እንዲህ አሉ፦ *"መልካም ቀን ፀሐይ ከወጣችበት የጁሙዓህ ቀን ነው÷ በዚያ ቀን አደም ተፈጠረ፣ በዚያ ቀን ወደ ጀነት ገብቷል÷ ከጀነት በዚያ ቀን ወጥቷል፣ ሰዓቲቱ በጁሙዓህ ቀን እንጂ አትቆምም"*። عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، أَنَّ النَّبِيَّ صلى الله عليه وسلم قَالَ " خَيْرُ يَوْمٍ طَلَعَتْ فِيهِ الشَّمْسُ يَوْمُ الْجُمُعَةِ فِيهِ خُلِقَ آدَمُ وَفِيهِ أُدْخِلَ الْجَنَّةَ وَفِيهِ أُخْرِجَ مِنْهَا وَلاَ تَقُومُ السَّاعَةُ إِلاَّ فِي يَوْمِ الْجُمُعَةِ "

አምላካችን አላህ በመሰብሰቢያውንም ቀን ሰውን ሁሉ ሰብሳቢ ነው÷ ጌታችን በመካከላችን ይሰበስባል። ከዚያም በመካከላችን በእውነት ይፈርዳል፦

3÷9 «ጌታችን ሆይ! *አንተ በእርሱ ለመምጣቱ ጥርጥር የሌለበት በኾነ ቀን ሰውን ሁሉ ሰብሳቢ ነህ*። ምንጊዜም አላህ ቀጠሮውን አያፈርስምና።» رَبَّنَا إِنَّكَ جَامِعُ النَّاسِ لِيَوْمٍ لَّا رَيْبَ فِيهِ ۚ إِنَّ اللَّهَ لَا يُخْلِفُ الْمِيعَادَ

34÷26 *«ጌታችን በመካከላችን ይሰበስባል። ከዚያም በመካከላችን በእውነት ይፈርዳል። እርሱም በትክክል ፈራጁ ዐዋቂው ነው»* በላቸው። قُلْ يَجْمَعُ بَيْنَنَا رَبُّنَا ثُمَّ يَفْتَحُ بَيْنَنَا بِالْحَقِّ وَهُوَ الْفَتَّاحُ الْعَلِيمُ

ትክክለኛ ፈራጅ እርሱ ብቻ ስለሆነ በዚያ ቀን ለፍርድ ይሰበስባል÷ ያ ቀን መምጣቱ ጥርጥር የለበትም። ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች ዐያውቁም፦

4÷26 *«አላህ ሕያው ያደርጋችኋል÷ ከዚያም ያሞታል። ከዚያም ወደ ትንሣኤ ቀን ይሰበስባችኋል÷ በእርሱ ጥርጥር የለበትም። ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች ዐያውቁም»* በላቸው። قُلِ اللَّهُ يُحْيِيكُمْ ثُمَّ يُمِيتُكُمْ ثُمَّ يَجْمَعُكُمْ إِلَىٰ يَوْمِ الْقِيَامَةِ لَا رَيْبَ فِيهِ وَلَـٰكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ
4÷87 አላህ ከእርሱ በስተቀር አምላክ የለም። *"ወደ ትንሣኤ ቀን በእርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲኾን በእርግጥ ይሰበስባችኋል"*። በንግግርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማነው? اللَّهُ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ ۚ لَيَجْمَعَنَّكُمْ إِلَىٰ يَوْمِ الْقِيَامَةِ لَا رَيْبَ فِيهِ ۗ وَمَنْ أَصْدَقُ مِنَ اللَّهِ حَدِيثًا

ነጥብ ስምንት

"የውሙል ፈስል"

"የውሙል ፈስል" يَوْمُ الْفَصْلِ ማለት የመለያው ቀን" ማለት ነው÷ የመለያው ቀን ለሁሉም ቀጠሯቸው ነው÷
44÷40 *"የመለያው ቀን" ለሁሉም ቀጠሯቸው ነው"*። إِنَّ يَوْمَ الْفَصْلِ مِيقَاتُهُمْ أَجْمَعِينَ

አምላካችን አላህ በመለያው ቀን አማንያንን ወደ ጀነት በማስገባት÷ ከሃድያንን ወደ እሳት በማስገባት በፍርድ ይለያል÷
32÷25 *ጌታህ እርሱ በዚያ በእርሱ ይለያዩበት በነበሩት ነገር በትንሣኤ ቀን በመካከላቸው በፍርድ ይለያል*። إِنَّ رَبَّكَ هُوَ يَفْصِلُ بَيْنَهُمْ يَوْمَ الْقِيَامَةِ فِيمَا كَانُوا فِيهِ يَخْتَلِفُونَ
22÷17 *እነዚያ ያመኑት፣ እነዚያም ይሁዳውያን የሆኑ፣ ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም፣ መጁሶችም፣ እነዚያም ያጋሩ አላህ በትንሣኤ ቀን በመካከላቸው በፍርድ ይለያል*። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ በእርግጥ ዐዋቂ

ነውና። إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَالَّذِينَ هَادُوا وَالصَّابِئِينَ وَالنَّصَارَىٰ وَالْمَجُوسَ وَالَّذِينَ أَشْرَكُوا إِنَّ اللَّهَ يَفْصِلُ بَيْنَهُمْ يَوْمَ الْقِيَامَةِ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ

ከሃድያን አስተባባዮች ስለሆኑ "ይህ ያ በእርሱ ታስተባብሉ የነበራችሁት "የመለያው ቀን" ነው" ይባላሉ፦

77÷14 *የመለያውም ቀን ምን እንደኾነ ምን አሳወቀህ?* وَمَا أَدْرَاكَ مَا يَوْمُ الْفَصْلِ

77÷15 ለአስተባባዮች በዚያ ቀን ወዮላቸው። وَيْلٌ يَوْمَئِذٍ لِّلْمُكَذِّبِينَ

37÷21 *«ይህ ያ በእርሱ ታስተባብሉ የነበራችሁት "የመለያው ቀን" ነው»* ይባላሉ። هَٰذَا يَوْمُ الْفَصْلِ الَّذِي كُنتُم بِهِ تُكَذِّبُونَ

ነጥብ ዘጠኝ

"የውመት -ተላቅ"

"የውመት ተላቅ" يَوْمَ التَّلَاقِ ማለት "የመገናኛውን ቀን" ማለት ነው፦

40÷15 *"እርሱ ደረጃዎችን ከፍ አድራጊ የዐርሹ ባለቤት ነው። "የመገናኛውን ቀን" ያስጠነቅቅ ዘንድ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ ከትዕዛዙ መንፈስን ያወርዳል*። رَفِيعُ الدَّرَجَاتِ ذُو الْعَرْشِ يُلْقِي الرُّوحَ مِنْ أَمْرِهِ عَلَىٰ مَن يَشَاءُ مِنْ عِبَادِهِ لِيُنذِرَ يَوْمَ التَّلَاقِ

ሰው አላህን ተገናኝቶ በሠራው ሰናይ ሥራ ወይም በሠራው እኩይ ሥራ ከጌታው ይተሳሰባል፦

84÷6 *"አንተ ሰው ሆይ! አንተ "ጌታህን እስከምትገናኝ" ድረስ ልፋትን ለፊ ነህ፦ "ተገናኚውም" ነህ"*። يَا أَيُّهَا الْإِنسَانُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدْحًا فَمُلَاقِيهِ

ሶላት መስገድ ጌታቸውን የሚገናኙ መኾናቸውን በዕውቀት የሚያረጋግጡ በኾኑት ላይ ቀላል ናት÷ ግን አላህን አግኝቹ ይተሳሰበኛል ብሎ እርግጠኛ ባልሆነ ላይ ግን ከባድ ናት÷
2÷46 *(ሶላት) እነዚያ "ጌታቸውን የሚገናኙ እነርሱም ወደ እርሱ ተመላሾች መኾናቸውን የሚያረጋግጡ በኾኑት ላይ እንጅ ከባድ ናት*።
الَّذِينَ يَظُنُّونَ أَنَّهُم مُّلَاقُو رَبِّهِمْ وَأَنَّهُمْ إِلَيْهِ رَاجِعُونَ

እኩያን ለእነርሱ÷ "ስገዱም" በተባሉ ጊዜ አይሰግዱም ነበር÷ ቅጣቱን ሲቀምሱ÷ ”ከሰጋጆቹ አልነበርንም" ይላሉ÷
77÷48 *"«ለእነርሱ ስገዱም» በተባሉ ጊዜ አይሰግዱም"*። وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ارْكَعُوا لَا يَرْكَعُونَ
74÷43 እነርሱም ይላሉ÷ *”ከሰጋጆቹ አልነበርንም”*። قَالُوا لَمْ نَكُ مِنَ الْمُصَلِّينَ

ነጥብ አስር

"የውሚል ሒሣብ"
"የውሚል ሒሣብ" يَوْمِ الْحِسَاب ማለት "የመተሳሰቢያ ወይም የምርመራ ቀን" ማለት ነው÷
38÷52 *"ይህ ለምርመራው ቀን የምትቀጠሩት ተስፋ ነው"*። هَٰذَا مَا تُوعَدُونَ لِيَوْمِ الْحِسَابِ

"ሒሣብ" حِسَاب የሚለው ቃል "ሐሢበ" حَسِبَ ማለትም "መረመረ" "ተቆጣጠረ" ተሳሰበ" ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "ምርመራ" "ቁጥጥር" "መተሳሰብ" "ማወራረድ" ማለት ነው። በቁርኣን ከተገለጹ

የአላህ ውብ ስሞች መካከል "አል-ሐሢብ" الْحَسِيب ሲሆን "ተቆጣጣሪ" "መርማሪ" "ተሳሳቢ" ማለት ነው፦

4÷86 በሰላምታ በተከበራችሁም ጊዜ ከእርሷ ይበልጥ ባማረ ሰላምታ አክብሩ። ወይም እርሷኑ መልሷት። *"አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ ነውና"*። وَإِذَا حُيِّيتُم بِتَحِيَّةٍ فَحَيُّوا بِأَحْسَنَ مِنْهَا أَوْ رُدُّوهَا ۗ إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ حَسِيبًا

2÷284 *በሰማያት ውስጥና በምድርም ውስጥ ያለው ሁሉ የአላህ ነው። በራሳችሁ ውስጥ ያለውን ብትገልጹ ወይም ብትደብቁት አላህ በእርሱ ይቆጣጠራችኋል*። لِّلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ ۗ وَإِن تُبْدُوا مَا فِي أَنفُسِكُمْ أَوْ تُخْفُوهُ يُحَاسِبْكُم بِهِ اللَّهُ

"ይቆጣጠራችኋል" ለሚለው የገባው ቃል "ዩሓሢብኩም" يُحَاسِبْكُم መሆኑ አንባቢ ልብ ይለዋል። በራሳችን ውስጥ ያለውን ብንገልጽ ወይም ብንደብቅ አምላካችን አላህ በእርሱ ማለትም በችሎታው ይቆጣጠረናል። እንዲሁ የፍርዱ ቀን ሰዎች የሠሩት ኸይር ሥራ፦ ወይም ሸር ሥራ ይተሳሰባል።

ነጥብ አሥራ አንድ

"የውመት -ተናድ"

"የውመት ተናድ" يَوْمَ التَّنَاد ማለት "የመጠራሪያን ቀን" ማለት ነው፦

40÷32 *«ሕዝቦቼ ሆይ! እኔ በእናንተ ላይ የመጠራሪያን ቀን እፈራለሁ»* አላቸው። وَيَا قَوْمِ إِنِّي أَخَافُ عَلَيْكُمْ يَوْمَ التَّنَادِ

"እፈራለው" ያለው በመጠራሪያን ቀን የሚኖረውን የመጨረሻውን ቀን ቅጣት ነው፦ "የመጨረሻውንም ቀን ፍሩ" ተብሏል፦

11÷103 *"በዚህ ውስጥ የመጨረሻውን ቀን ቅጣት ለሚፈሩ ሁሉ መገሰጫ አለ"*። إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَةً لِّمَنْ خَافَ عَذَابَ الْآخِرَةِ
29÷36 ወደ መድየንም ወንድማቸውን ሹዐይብን ላክን፦ *«ሕዝቦቼ ሆይ! አላህን አምልኩ! "የመጨረሻውንም ቀን" ፍሩ! በምድርም ውስጥ የምታጠፉ ሆናችሁ አታበላሹ»* አላቸውም። وَإِلَىٰ مَدْيَنَ أَخَاهُمْ شُعَيْبًا فَقَالَ يَا قَوْمِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَارْجُوا الْيَوْمَ الْآخِرَ وَلَا تَعْثَوْا فِي الْأَرْضِ مُفْسِدِينَ

"በእናንተ ላይ የመጠራረያን ቀን" የሚለው ኃይለ-ቃል ይሰመርበት።
ሕዝቦቼ በክህደት ከቀጠሉ እና የእሳት ሰዎች ከሆኑ የጀነት ሰዎች የእሳትን ሰዎችን፦ "ጌታችን ቃል የገባልንን እውነት ኾኖ አገኘን፥ ጌታችሁ የዛተባችሁንስ እውነት ኾኖ አገኛችሁትን? ሲሉ ይጣራሉ፦
7÷44 *"የጀነትም ሰዎች የእሳትን ሰዎችን «ጌታችን ቃል የገባልንን እውነት ኾኖ አገኘን፥ ጌታችሁ የዛተባችሁንስ እውነት ኾኖ አገኛችሁትን?» ሲሉ "ይጣራሉ"*። «አዎን አገኘን» ይላሉ።
በመካከላቸውም «የአላህ ርግማን በበደለኞች ላይ ይኹን» ሲል ለፋሪ ይለፍፋል። وَنَادَىٰ أَصْحَابُ الْجَنَّةِ أَصْحَابَ النَّارِ أَن قَدْ وَجَدْنَا مَا وَعَدَنَا رَبُّنَا حَقًّا فَهَلْ وَجَدتُّم مَّا وَعَدَ رَبُّكُمْ حَقًّا ۖ قَالُوا نَعَمْ ۚ فَأَذَّنَ مُؤَذِّنٌ بَيْنَهُمْ أَن لَّعْنَةُ اللَّهِ عَلَى الظَّالِمِينَ

"ይጣራሉ" የሚለው ይሰመርበት። በጀነት ሰዎች እና በእሳትን ሰዎች መካከል ግርዶች አለ፥ ይህ ቦታ "አዕራፍ" أَعْرَاف ይባላል። በዚህ ቦታ ሰናይና እኩይ ሥራቸው በሚዛን እኩል የሆኑት ሰዎች "አስሓቡል አዕራፍ" أَصْحَابُ الْأَعْرَاف ይባላሉ፥ የጀነት ሰዎች የአዕራፍ ሰዎችን፦ "ሰላም ለእናንተ ይኹን" በማለት ይጣራሉ፦
7÷46 በመካከላቸውም ግርዶሽ አልለ። በአዕራፍም ላይ ሁሉንም በምልክታቸው የሚያውቁ ሰዎች አሉ። የግኑትንም ሰዎች ሰላም ለእናንተ ይኹን በማለት ይጣራሉ። እነርሱም የአዕራፍ ሰዎች የሚከጅሉ ሲኾኑ ገና

አልገቧትም። وَبَيْنَهُمَا حِجَابٌ ۚ وَعَلَى الْأَعْرَافِ رِجَالٌ يَعْرِفُونَ كُلًّا بِسِيمَاهُمْ ۚ وَنَادَوْا أَصْحَابَ الْجَنَّةِ أَن سَلَامٌ عَلَيْكُمْ ۚ لَمْ يَدْخُلُوهَا وَهُمْ يَطْمَعُونَ

ነጥብ አሥራ ሁለት

"የውሙል ወዒድ"

"የውሙል ወዒድ" يَوْمُ الْوَعِيد ማለት "የዛቻው ቀን" ማለት ነው፦

50÷20 *"በቀንዱም ውስጥ ይነፋል፥ ያ ቀን የዛቻው ቀን ነው"*። وَنُفِخَ فِي الصُّورِ ۚ ذَٰلِكَ يَوْمُ الْوَعِيدِ

በሃይማኖት ማስገደድ የለም፥ ቅኑ መንገድ ከጠማማው ተገልጧል።
የሻም ሰው ይመን፥ የሻም ሰው ይካድ፦

2÷256 *በሃይማኖት ማስገደድ የለም፥ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ*። لَا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ ۖ قَد تَّبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ

18÷29 *«እውነቱም ከጌታችሁ ነው። የሻም ሰው ይመን፥ የሻም ሰው ይካድ»* በላቸው። وَقُلِ الْحَقُّ مِن رَّبِّكُمْ ۖ فَمَن شَاءَ فَلْيُؤْمِن وَمَن شَاءَ فَلْيَكْفُرْ

"የሻም ሰው ይመን፥ የሻም ሰው ይካድ" ማለት ዛቻ ነው። በግድ እምኑ በማለት በእነርሱ ላይ አስገዳጅ አይደለንም፥ የአላህ ዛቻ የሚፈራን ሰው በቁርኣን ማስታወስ ብቻ ነው፥ ከዚያም በዛቻው ቀን የገነትም ሰዎች የእሳትን ሰዎችን፦ ጌታችሁ "የዛተባችሁንስ" እውነት ኾኖ አገኛችሁትን? ሲሉ ይጣራሉ፦

50÷45 እኛ የሚሉትን ሁሉ ዐዋቂ ነን። *"አንተም በእነርሱ ላይ አስገዳጅ አይደለህም። ስለዚህ ዛቻዬን የሚፈራን ሰው በቁርኣን አስታውስ*። نَّحْنُ أَعْلَمُ بِمَا يَقُولُونَ ۖ وَمَا أَنتَ عَلَيْهِم بِجَبَّارٍ ۖ فَذَكِّرْ بِالْقُرْآنِ مَن يَخَافُ وَعِيدِ

7÷44 *"የገነትም ሰዎች የእሳትን ሰዎችን «ጌታችን ቃል የገባልንን እውነት ኾኖ አገኘን÷ ጌታችሁ "የዛተባችሁንስ" እውነት ኾኖ አገኛችሁትን?» ሲሉ "ይጣራሉ"*። «አዎን አገኘን» ይላሉ። በመካከላቸውም «የአላህ ርግማን በበደለኞች ላይ ይኹን» ሲል ለፋሪ ይለፍፋል። وَنَادَىٰ أَصْحَابُ الْجَنَّةِ أَصْحَابَ النَّارِ أَن قَدْ وَجَدْنَا مَا وَعَدَنَا رَبُّنَا حَقًّا فَهَلْ وَجَدتُّم مَّا وَعَدَ رَبُّكُمْ حَقًّا ۖ قَالُوا نَعَمْ ۚ فَأَذَّنَ مُؤَذِّنٌ بَيْنَهُمْ أَن لَّعْنَةُ اللَّهِ عَلَى الظَّالِمِينَ

አላህ በቁርኣን ዝቶበት የነበረው ቀን ሲመጣ ያ ቀን የዛቻው ቀን ነው። ካፊሮች አንዱ ሌላውን በመውቀስ ሲጨቃጨቁ አላህ÷ "ወደ እናንተ ዛቻን በእርግጥ ያስቀደምኩ ስኾን እኔ ዘንድ አትጨቃጨቁ" ይላቸዋል÷ ቀድሞውኑ አላህ÷ "እኛ ለበደለኞች አጥሯ በእነርሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል÷ ከጥም እርዳታንም ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ። መጠጡ ከፋ÷ መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች" ብሎ ተናግሯል÷
50÷28 *"አላህ «ወደ እናንተ ዛቻን በእርግጥ ያስቀደምኩ ስኾን እኔ ዘንድ አትጨቃጨቁ» ይላቸዋል*። قَالَ لَا تَخْتَصِمُوا لَدَيَّ وَقَدْ قَدَّمْتُ إِلَيْكُم بِالْوَعِيدِ
18÷29 *«እውነቱም ከጌታችሁ ነው። የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው። እኛ ለበደለኞች አጥሯ በእነርሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል÷ ከጥም እርዳታንም ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ። መጠጡ ከፋ÷ መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች*። وَقُلِ الْحَقُّ مِن رَّبِّكُمْ ۖ فَمَن شَاءَ فَلْيُؤْمِن وَمَن شَاءَ فَلْيَكْفُرْ ۚ إِنَّا أَعْتَدْنَا لِلظَّالِمِينَ نَارًا أَحَاطَ بِهِمْ سُرَادِقُهَا ۚ وَإِن يَسْتَغِيثُوا يُغَاثُوا بِمَاءٍ كَالْمُهْلِ يَشْوِي الْوُجُوهَ ۚ بِئْسَ الشَّرَابُ وَسَاءَتْ مُرْتَفَقًا

ነጥብ አሥራ ሦስት

የውመል ሐሥራህ"

"የውመል ሐሥራህ" يَوْمَ الْحَسْرَةِ ማለት "የቁልጭቱን ቀን" ማለት ነው፦

19÷39 *እነርሱም አሁን በዝንጋቴ ላይ ኾነው ሳሉ እነርሱም የማያምኑ ሲኾኑ ነገሩ በሚፈረድበት ጊዜ "የቁልጭቱን ቀን አስጠንቅቃቸው*።

وَأَنذِرْهُمْ يَوْمَ الْحَسْرَةِ إِذْ قُضِيَ الْأَمْرُ وَهُمْ فِي غَفْلَةٍ وَهُمْ لَا يُؤْمِنُونَ

በዚህ ቀን ኩፋሮች በቁጭት ከሚሉት መካከል፦ “ከመልክተኛው ጋር ቀጥተኛን መንገድ ይዤ በኾነ ዋ ምኞቴ” “አላህን በተገዛን መልክተኛውንም በታዘዝን ኖሮ” በማለት ይቆጫሉ። ኩፋሮች ከቁጭትዋ የተነሳ ሲቆጩ የእሳት ዘበኞች፦ “አስጠንቃቂ አልመጣችሁምን?” በማለት ይጠይቋቸዋል፦

25÷27 *በዳይም «ከመልክተኛው ጋር ቀጥተኛን መንገድ ይዤ በኾነ ዋ ምኞቴ!» እያለ በጸጸት ሁለት እጆቹን የሚነክስበትን ቀን አስታውስ*።

وَيَوْمَ يَعَضُّ الظَّالِمُ عَلَىٰ يَدَيْهِ يَقُولُ يَا لَيْتَنِي اتَّخَذْتُ مَعَ الرَّسُولِ سَبِيلًا

33÷66 ፊቶቻቸው በእሳት ውስጥ በሚገለባበጡ ቀን *«ዋ ምኞታችን! አላህን በተገዛን መልክተኛውንም በታዘዝን ኖሮ» እያሉ ይጸጸታሉ*። يَوْمَ تُقَلَّبُ وُجُوهُهُمْ فِي النَّارِ يَقُولُونَ يَا لَيْتَنَا أَطَعْنَا اللَّهَ وَأَطَعْنَا الرَّسُولَا

67÷8 *ከቁጭትዋ የተነሳ ልትቆራረጥ ትቀርባለች። በውስጧ ጭፍሮች በተጣሉ ቁጥር ዘበኞችዋ *«አስጠንቃቂ አልመጣችሁምን?*» በማለት ይጠይቋቸዋል። تَكَادُ تَمَيَّزُ مِنَ الْغَيْظِ ۖ كُلَّمَا أُلْقِيَ فِيهَا فَوْجٌ سَأَلَهُمْ خَزَنَتُهَا أَلَمْ يَأْتِكُمْ نَذِيرٌ

ኩፋሮች ይህንን መልእክት ተቀብለው ከሙሥሊሞች ጋር በመሆን አንዱን አምላክ ማምለክ ሲገባቸው የተውበት በሩ ከተዘጋ በኃላ በቁጭቱ ቀን፦ “ታላቅ ዕድልን አገኝ ዘንድ ከእነርሱ ጋር በኾንኩ ወይ ምኞቴ” “ዋ እኔ! ምነው በሕይወቴ መልካምን ሥራ ባስቀደምኩ ኖሮ” “ዋ ምኞቴ!

ምንነው ዐፈር በኾንኩ” “ዋ ጥፋቴ! እገሌን ወዳጅ ባልያዝኩ ኖሮ እመኛለሁ” ይላሉ፦

4÷73 ከአላህም የኾነ ችሮታ ቢያገኛችሁ በእናንተና በእርሱ መካከል ፍቅር እንዳልነበረች ሁሉ *«ታላቅ ዕድልን አገኝ ዘንድ ከእነርሱ ጋር በኾንኩ ወይ ምኞቴ!»* ይላል። وَلَئِنْ أَصَابَكُمْ فَضْلٌ مِّنَ اللَّهِ لَيَقُولَنَّ كَأَن لَّمْ تَكُن بَيْنَكُمْ وَبَيْنَهُ مَوَدَّةٌ يَا لَيْتَنِي كُنتُ مَعَهُمْ فَأَفُوزَ فَوْزًا عَظِيمًا

89÷24 *«ዋ እኔ! ምነው በሕይወቴ መልካምን ሥራ ባስቀደምኩ ኖሮ»* ይላል። يَقُولُ يَا لَيْتَنِي قَدَّمْتُ لِحَيَاتِي

78÷40 እኛ ሰው ሁሉ እጆቹ ያስቀደሙትን በሚያይበትና ከሓዲውም፦ *ዋ ምኞቴ! ምንነው ዐፈር በኾንኩ* በሚልበት ቀን ቅርብ የኾነን ቅጣት አስጠነቀቅናችሁ። إِنَّا أَنذَرْنَاكُمْ عَذَابًا قَرِيبًا يَوْمَ يَنظُرُ الْمَرْءُ مَا قَدَّمَتْ يَدَاهُ وَيَقُولُ الْكَافِرُ يَا لَيْتَنِي كُنتُ تُرَابًا

25÷28 *«ዋ ጥፋቴ! እገሌን ወዳጅ ባልያዝኩ ኖሮ እመኛለሁ*። يَا وَيْلَتَىٰ لَيْتَنِي لَمْ أَتَّخِذْ فُلَانًا خَلِيلًا

ነጥብ አሥራ አራት

"የውሙም መሽሁድ"

"የውሙም መሽሁድ" دُوعَشْمَّ يَوْمٌ ማለት "የሚመሰከሩበት ቀን" ማለት ነው፦

11÷103 *በዚህ ውስጥ የመጨረሻውን ቀን ቅጣት ለሚፈሩ ሁሉ መገሰጫ አለ። ይህ የትንሣኤ ቀን ሰዎች በእርሱ የሚሰበሰቡበት ቀን ነው። ይህም የሚመሰከሩበት ቀን ነው"*። ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَةً لِّمَنْ خَافَ عَذَابَ الْآخِرَةِ ذَٰلِكَ يَوْمٌ مَّجْمُوعٌ لَّهُ النَّاسُ وَذَٰلِكَ يَوْمٌ مَّشْهُودٌ

በቁርኣን አናቅጽ ላይ “ሻሂድ” ሸَاهِد ማለት የሚመሰክር “መስካሪ” ማለት ሲሆን “መሽሁድ” مَشْهُود ማለት ደግሞ የሚመሰከርበት “ተመስካሪ” ማለት ነው። በተቀጠረው ቀን መስካሪ በተመስካሪ ላይ ይመሰክራሉ፦

85÷2 *”በተቀጠረው ቀንም እምላለው”*። وَالْيَوْمِ الْمَوْعُودِ

85÷3 *”በመስካሪ እና በተመስካሪ እምላለሁ”*። وَشَاهِدٍ وَمَشْهُودٍ

“መስካሪ” የተባሉት “ነቢያት” ሲሆኑ “የሚመሰከርባቸው” ደግሞ “ኡማቸው” ናቸው፦

16÷84 *”ከየሕዝቡም ሁሉ መስካሪን የምንቀሰቅስበትን ቀን አስታውስ”*። وَيَوْمَ نَبْعَثُ مِن كُلِّ أُمَّةٍ شَهِيدًا

4÷41 *”ከሕዝቦችም ሁሉ መስካሪን ባመጣን ጊዜ አንተንም በእነዚህ ሕዝብ ላይ መስካሪ አድርገን በምናመጣህ ጊዜ የከሓዲዎች ኹኔታ እንዴት ይኾን?”* فَكَيْفَ إِذَا جِئْنَا مِن كُلِّ أُمَّةٍ بِشَهِيدٍ وَجِئْنَا بِكَ عَلَىٰ هَٰؤُلَاءِ شَهِيدًا

16÷89 *”በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ ከራሳቸው በእነርሱ ላይ መስካሪን የምንቀሰቅስበትን አንተንም በእነዚህ ሕዝብ ላይ መስካሪ አድርገን የምናመጣህን ቀን አስታውስ”*። وَيَوْمَ نَبْعَثُ فِي كُلِّ أُمَّةٍ شَهِيدًا عَلَيْهِم مِّنْ أَنفُسِهِمْ ۖ وَجِئْنَا بِكَ شَهِيدًا عَلَىٰ هَٰؤُلَاءِ

28÷75 *”ከሕዝቦችም ሁሉ መስካሪን እናወጣለን። ያን ጊዜ እውነተኞውም አምላክነት ለአላህ ብቻ መኾኑን ያውቃሉ። ይቀጣጥፉት የነበሩትም ከእነርሱ ይጠፋቸዋል”*። وَنَزَعْنَا مِن كُلِّ أُمَّةٍ شَهِيدًا فَقُلْنَا هَاتُوا بُرْهَانَكُمْ فَعَلِمُوا أَنَّ الْحَقَّ لِلَّهِ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُوا يَفْتَرُونَ

“ኡማህ” أُمَّة ማለት “ሕዝብ” ማለት ሲሆን በአንድ ነቢይ ዘመነ-መግቦት”dispensation” የሚቆዩትን “ሰዎች” ያመለክታል። እያንዳንዱ ነቢይ በራሱ ኡማህ ላይ በትንሳኤ ቀን ይመሰክራሉ።

አሥራ አምስት

"የውሙል ኹሉድ"

ኹሉድ" خُلُود የሚለው ቃል "ኸለደ" خَلَدَ ከሚለው ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "ዘላለማዊነት" ማለት ነው÷ "የውሙል ኹሉድ" يَوْمُ الْخُلُود ማለት "የዘላለማዊነት ወይም የመዘውተሪያ ቀን" ማለት ነው÷
50÷34 *"«በሰላም ግቢት ይህ "የመዘውተሪያ ቀን" ነው»* ይባላሉ።
ادْخُلُوهَا بِسَلَامٍ ۖ ذَٰلِكَ يَوْمُ الْخُلُودِ

የትንሳኤ ቀን የጀነት ባለቤቶች በጀነት ውስጥ ለዘላለም ይኖራሉ÷ የእሳት ባለቤቶች በእሳት ውስጥ ለዘላለም ይኖራሉ። ሞት ይጠፋል÷
ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 81, ሐዲስ 134
አቡ ሁራይራህ እንደተረከው÷ "ነቢዩ"ﷺ" እንዲህ አሉ÷ *"ለጀነት ባለቤቶች÷ "ለእናንተ ዘላለማዊነት እንጂ ሞት የለም" ይባላሉ÷ ለእሳት ባለቤቶች÷ "ለእናንተ ዘላለማዊነት እንጂ ሞት የለም" ይባላሉ"*። عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، قَالَ قَالَ النَّبِيُّ صلى الله عليه وسلم " يُقَالُ لأَهْلِ الْجَنَّةِ خُلُودٌ لاَ مَوْتَ. وَلأَهْلِ النَّارِ يَا أَهْلَ النَّارِ خُلُودٌ لاَ مَوْتَ "

"ኻሊድ" خَالِد ማለት "ዘላለማዊ" "ዘውታሪ" ማለት ነው÷ የኻሊድ ብዙ ቁጥር ደግሞ "ኻሊዲን" خَالِدِين ወይም "ኻሊዱን" خَالِدُون ሲሆን "ዘላለማውያን" ወይም "ዘውታሪያን" ማለት ነው። በጀነት የሚኖሩ አማንያን "አስሓቡል ጀናህ" أَصْحَابُ الْجَنَّة ማለትም "የገነት ጓዶች" ሆነው ለዘላለም ይኖራሉ÷
2÷82 *እነዚያም ያመኑት በጎ ሥራዎችንም የሠሩት እነዚያ የገነት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ናቸው*። وَالَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ أُولَٰئِكَ أَصْحَابُ الْجَنَّةِ ۖ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ

በተቃራኒው ጀሀነም የሚኖሩ ከሃድያን "አስሓቡን ናር" أَصْحَابُ النَّار ማለትም "የእሳት ጓዶች" ሆነው ለዘላለም ይኖራሉ፦
2÷39 *እነዚያም በመልክተኞቻችን የካዱ በአንቀጾቻችንም ያስተባበሉ እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው*።
وَالَّذِينَ كَفَرُوا وَكَذَّبُوا بِآيَاتِنَا أُولَـئِكَ أَصْحَابُ النَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَالِدُونَ

የአላህ ዘላለማዊነት መነሻ የሌለው ቀዳማይ፦ መዳረሻ የሌለው ደኃራይ ነው። በጀነት እና በጀሀነም ያሉትን መነሻ ያላቸው ስለሆኑ ዘላለማዊነታቸው ቂደም አይደለም፦ "ቂደም" قِدَم የሚለው ቃል "ቀዱመ" قَدُمَ ከሚለው ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "ጅማሬ ወይም መነሻ የሌለው ቀዳማዊ ዘላለም"pre eternity" ማለት ነው፦ ይህ ዘላለማዊነት የአላህ ብቻ ነው።
ነገር ግን በጀነት እና በጀሀነም ያሉትን ዘላለማዊነታቸው በቃእ ነው፦ "በቃእ" ءَبَقَا የሚለው ቃል "በቂየ" بَقِيَ ከሚለው ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን ፍጻሜ ወይም መዳረሻ የሌለው ደኃራዊ ዘላለም"post eternity" ማለት ነው። ስለ የመጨረሻው ቀን እሳቤ ከብዙ በጥቂቱ ይኸን ይመስላል።
አምላካችን አላህ ዒባዳችንን በኢኽላስ ተቀብሎ አስሓቡል ጀናህ ከሚላቸው ባሮቹ ያድርገን! አሚን።

ከወንድም ወሒድ ዑመር

https://t.me/Wahidcom

ወሠላሙ ዐለይኩም